ስለዚህ ይህንን አምባገነን ስርዓት ታግለን ለመጣል የግዴታ እያንዳንዱ ዜጋ እስር ቤት ገብቶ መታሰርን እና መገረፍን መመልከትሳይሆን ወንድም እህቶቻችን በእስር ቤት ያሳለፉት መከራ እንደመከራችን አይተን ሲነጋ ደግሞ ወደ እኛ ቤት እንደሚመጣአስበን ያለአግባብ ለታሰሩት ሃቀኛ ፍትህን ለኛም የማይሸራርፍ ሰብአዊ መብቶቻችንን ለማግኘት መታገል ግዴታችን መሆኑንማወቅ ያስፈልገናል። ለዘመናት ተሳስሮ እና ተከባብሮ የኖረን ህዝብ ለማፋጀት ዘመን በወለዳቸው የዘመኑ ቋንቋ "አሸባሪ" ወይ"አክራሪ" እየተባሉ ዜጎች የሚደርስባቸው መከራ እንዲቆም እያንዳንዳችን የበኩላችንን በማድረግ የድርሻችንን ማበርከት አለብን።የአብሮነታችን ተምሳሌት ለአለም ያስተማረውን የአያቶቻችንን የአንድነት ወዳድነትን ደግመን ለወያኔው መንግስት ማሳየት አለብን። አምባገነኖችን ጠንክረን ከታገልናቸው ቀዳዳው ሁሉ ስለሚጠብባቸው ተፍረክርከው ይጠፋሉ። ሃገራችን እና ወገናችንበጨለማ ውስጥ እየዳከረ ባለበት በዚህ የወያኔ አገዛዝ ወቅት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በመረባረብ የዜግነት ግዴታውን አውቆለህዝቦች መብት እና ለሃገር ነጻነት መታገል አለበን።

ወያኔን ለአንዴና ለመጨረሻ አንኮታኩቶ ለመጣል ሁላችንም የአንድነት ሃይሎች ከተከባበርን፣ ከተደማመጥን፣ ከተስማማንናከተባበርን ለውጥ ለማምጣት ፈቃደኝነቱና ቆራጥነቱ ካለን ለጋራ ዓላማ ለህዝብ ነጻነትና ለእኩልነት ትግሉን በአንድነትእንቀርጻለን፣ በጋራ እንቆምለታለን፣ በጋራ ከምንፈልገው ግብ አብረን እንደርሳለን ካልን አገራችንን ከጥፋትና አደጋ፣ ህዝባችንንምከሥቃይና መከራ በቶሎ እንታደጋለን ማለት ነው ፡፡ ለዚህ ደግሞ ቀጣይ ትግላችን በነጠረ ዓላማና በህዝባዊ መሰረት ላይየቆመ/የተገነባ መሆኑን እርግጠኛ መሆን የሚገባን፡፡ መሪዎች የሚወጡት ከህዝብ ውስጥ እንደመሆኑ ህዝብን አደራጅቶ የትግሉአካልና ንቁ ተዋናይ የማድረግና ለዚህም ወደ ህዝቡ ተደራሽነታችንን የማስፋት ተግባራት ከፊታችን ይጠብቁናል ማለት ነው፡፡ስለሆነም የጋራ ጠላታችንን በአንድነት ሆነን የአቅማችንን በማድረግ ለእናት ኢትዮጵያ እንድረስላት፡፡

ሌላው በመናገርና በመጻፍ እንዲሁም ሃሳብን በነጻነት መግለጽ የተከለከለባት ሃገራችን ጋዜጠኝነት እንደወንጀልና አሸባሪነትከተፈረጀ ከረምረም ብሏል፣ "ጋዜጠኝነትን እና የፖለቲካ ድርጅትን ሽፋን በማድረግ የሀገሪቱንና የሕዝቦቿን ሰላም ለማደፍረስከሚያስቡና ከሚፈልጉ 'ሀይላት' ጋር ግንኙነት በማድረግ፣ህገ-መንግስቱን በሃይል ለመናድ የተለያዩ የሽብር ተግባራትን ለመፈጸምሲንቀሳቀሱ በቁጥጥር ስር አውለናቸዋል።" ይህ አባባል የወያኔ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ 652/2001 እንደ ካብ ድንጋይየተደረደረ ይመስል "ህገ-መንግስትን ለመናድ" የምትል ተደጋጋሚ ማስፈራሪያ ትሁን ቀልድ ያልታወቀች አባባል መስማትየተለመደ ሆኗል፡፡ ይህች ሃረግ የኢትዮጵያ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ 652/2001 ከወጣበት ከነሀሴ 2001 ዓ.ም. ጀምሮጋዜጠኞችና በሰላማዊ መንገድ ተመዝግበው የፖለቲካ ምህዳሩን የተቀላቀሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት በወያኔ መራሹ ቡድንከታሰሩ በኋላ በመንግስት አካላት የሚሰጥ የተለመደ የመወንጀያ አባባል ነው። የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮእስከ መስከረም 2007 ዓ.ም ባሉት አምስት ዓመታት ውስጥም ከጋዜጠኛ እስከ ፖለቲከኛ፣ ከሀይማኖት መሪዎች እስከጦማሪያን፣ ከታጣቂ ወታደሮች እስከ የኮንትሮባንድ ነጋዴዎች በዚሁ አዋጅ አማካኝነት 'ሽብርተኝነታቸው ተረጋግጦላቸዋል'ወይም 'ይረጋገጥባቸው ዘንድ ፍርዳቸውን እየጠበቁ ይገኛሉ።' ለመሆኑ ይህ ከ14 ዓመት ህፃን እስከ 80 ዓመት አዛውንትበሽብርተኝነት ወንጀል ክስ የሚያስቀጣው፣ ይህ ከምሁራን እስከ ገበሬዎች ድረስ የሚያስረው ዜጎችን የሚያሰቃየው ሰነድየህዝብን የመናገርና ሃሳብን የመግለጽ መብት በእጅጉ የሸበበና በተጨባጭ መንግስት እንደፈለገ እያመካኘ ህዝብንና ንጹሃንዜጎችን እንዲያንገላታና እንዲያሰቃይ ትልቅ በር የከፈተ የአምባገነኖች መሳርያ ሆኖ እያገለገለ ነው።

ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አንዱ ለሌላው መረጃዎችን በማስተላለፍ ወያኔ እና ሚዲያዎቹ የሚጠቀሙበትን የማደናበሪያናየማደናገርያ ስልት በማጋለጥ እና ሊደናበር የሚችለውን የዋሁን ኢትዮጵያዊ በማስረዳት የዜግነት ግዴታችንን እየተወጣን በጋራበመታገል ይህንን ውሸታም እና አጭበርባሪ አደናባሪ ዘረኛ ስርአት ልናስወግደው እና ለመጪው ትውልድ እውነትን የተሞላችከአባቶቻችን በደምና በአጥንት የተከበረችውን ውዲቱን ሃገራችንን ለተተኪው ትውልድ የማስረከብ ሃላፊነት እንዳለብንለማሳሰብ እወዳለሁ። በጋራና በአንድነት ከአንድነት ሃይሎች ጋር በመታገል ቀጣይ ድሎቻችንን ለኢትዮጵያ ህዝብ እናመጣለን፣ሃገራችን በዚህ አደጋ ውስጥ ባለችበት ሰአት ላይ ህዝብ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ለኑሮ ውድነት፣ ለሞት፣ ለስደትና ለኢሰብአዊድርጊቶች እየተዳረገ እንዲሁም ኢትዮጵያዊነት እየተዋረደ ከመሆኑም ባሻገር ሃገሪቷን ወደ ፍርስራሽነት ለመቀየር የሚሮጡ ጥቂትዘረኞች ኢትዮጵያን ከመበታተንና ህዝቧንም ከማጥፋት ልናቅባቸውና ባሉበት ልንቀብራቸው ይገባል። መላው ኢትዮጵያውያንለዚህ አሸባሪ እና አጭበርባሪ አደናጋሪ መንግስታዊ አክራሪ ሳንዘናጋ በጋራ ተያይዘን በአንድ ሃገራዊ አጀንዳ አምባገነኖችንበመቅበር በእጃችን ያለውን ነጻነት በማረጋገጥ ለገነው ትውልድ አዲሲቷን የጋራ ኢትዮጵያችንን በማስረከብ ታላቅ የሆነውንየዜግነት ድርሻችንን እና ሃላፊነታችንን እንድንወጣ ለማሳሰብ እወዳለሁ::